ቁጥር፡ ስ/አ/ጽ/ቤት 51/12
ቀን: 24/02/2012 ዓ.ም

ለ፦ ቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ የጉ/ሥ/ሥ/ አ/የስራ ሂደት
ለ፦ ኢስተርን ኢንዱስትሪ ፓርክ የጉ/ሥ/ሥ/ አ/የስራ ሂደት
ለ፦ ወጪና ንግድ ያልሆኑ ገቢ ዕቃዎች አወጣጥ የስራ ሂደት
ለ፦ የንግድ ገቢ ዕቃዎች አወጣጥ የስራ ሂደት
ለ፦ ገላን ጉምሩክ መቅረጫ ጣቢያ
ለ፦ ኢንተለጀንስና ኮንትሮባንድ ክትትል የስራ ሂደት
ለ፦ እንዶዴ ባቡር ጣቢያ የጉ/ሥ/ሥ/ አ/የስራ ሂደት

ከ፦ ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
አ.አ. ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

አለማየሁ አንቲቾ ደዴቦ
ስራ አስኪያጅ
Alemayehu Anticho dedebo
Manager

ጉዳዩ፦ የቀረጥና ታክስ ነፃ አፈቃቀድን ይመለከታል፤

የጉምሩክ ኮሚሽን ጽ/ቤት በቁጥር 4/0267/12 በቀን 21/02/2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ቀደም ሲል በቁጥር 4/0255/12 በቀን 15/02/2012 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ በጉምሩክ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የቀረጥና ታክስ ነጻ መብት እንዲፈቅዱ በህግ ለሌሎች የመንግስት አካላት ተሰጥቶ የነበረው ሥልጣን ለገንዘብ ሚኒስቴር መተላለፉ የተደነገገ ስለሆነ ከዚሁ ድንጋጌ ውጭ በማናቸውም የመንግስት አካላት ተፈቅደው ለሚቀርቡ የቀረጥ ነጻ መብቶች አገልግሎት የማንሰጥ መሆኑ ታውቆ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ተፈቅደው ለሚቀርቡ ጉዳዮች ብቻ አገልግሎት እንዲሰጥ ማሳወቁን በማስታወስ፡፡ ነገር ግን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ቀ/ነ/ተ/14/4/138 በቀን 19/02/20112 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ ለኢንቨስትመንት ስለሚሰጡ ማበረታቻዎችና ማበረታቻዎቹን የሚፈቀዱበትን የአሰራር ስርዓት የሚወስንና አሁን የሚሰራበትን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ የሚተካ ደንብ በሚኒስቴሮች ም/ቤት ፀድቆ በስራ ላይ እስኪውል እና እንደአስፈላጊነቱ ደንቡን የሚያስፈጽሙ መመሪያዎች እስኪወጡ ድረስ የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ጥያቄዎች ተቀብሎ በስራ ላይ ባለው ደንብና መመሪያዎች መሠረት ለኢንቨስትመንት ማበረታቻ ብቁ ለሆኑ ባለሃብቶች ማበረታቻ እንዲፈቀድ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተወከለ መሆኑን ያሳወቀበትን አሳውቆናል፡፡

ስለሆነም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 6 በወሰነው መሠረት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ለኢንቨስትመንት ማበረታቻ ብቁ ለሆኑ ባለሃብቶች ማበረታቻ እንዲፈቅድ የተወከለ ስለሆነ በኮሚሽኑ ለሚፈቀዱ ማበረቻዎች አገልግሎት እንዲሰጥ እያሳሰብኩ ለአፋጻጸም ይረዳችሁ ዘንድ ከኮሚሽናችን የተላከ 1ገጽ ኮፒ ደብዳቤ አባሪ ተደርጓል፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ
ለ፦ ም/ስራ አስኪያጅ (አምራች ወጪና ሌሎች ጣቢያዎች)
ለ፦ ም/ስራ አስኪያጅ (የንግድ ገቢ ዕቃዎች ኦፕሬሽን)
ለ፦ ም/ስራ አስኪያጅ (ህግ ተገዥነት)
ለ፦ ም/ስራ አስኪያጅ (አቅምና ድጋፍ)
ለ፦ ደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ የስራ ሂደት
ለ፦ ድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የስራ ሂደት
አ.አ. ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

